የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፪
አዲስ አበባ መስከረም ፲ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

FIFTH YEAR NO.52
ADDIS ABABA 20TH SEPTEMBER, 2012

**ማውጫ**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ ዙ-ፓርክ ማዕከል ደንብ..............................ገፅ ፮፻፪

**CONTENTS**

The Addis Ababa City Government Addis Zoo Park Center Regulation………………..Page 602

## ደንብ ቁጥር ፶፪/፪ሺ፭ ዓ.ም

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ ዙ-ፓርክ ማዕከል ለማቋቋም የወጣ ደንብ

የከተማውን የቱሪዝም ኢኮኖሚ ለማበልፀግ፣ ትምህርት ለመስጠትና የምርምር ስራ ለማካሄድ እንዲሁም የአገሪቷን ብርቅዬ የዱር እንስሳት በዘመናዊነት በተደራጀ መልኩ እንክብካቤና ጥበቃ ለማድረግ በተለይም ዝርያቸው በመጥፋት ላይ ያሉትን ዘራቸውን ለማራባትና ቁጥራቸው እንዲጨምር ማድረግ በማስፈለጉ፤

ከከተማው ህዝብ ቁጥር ጋር ተያይዞ እያሻቀበ የመጣውን የጎብኚዎች ቁጥር በአግባቡ ለማስተናገድ እንዲሁም የከተማውን ነዋሪ የመዝናኛ ፍላጎት ማሟላት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፫(፩) (ረ) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## Regulation No. 52/2012

## A Regulation to Provide for the Establishment of Addis Zoo Park Center in the Addis Ababa City Government

**WHEREAS,** it is found necessary to develop the City's tourism economy, to create conducive atmosphere for research and education, to arrange well organized modern park for wild life particularly to reproduce and increase the number of endemic animals and others on the way of extinction;

**WHEREAS**, it is found necessary to accommodate the ever increasing number of visitors due to growth of population of the City and to fulfill the recreation demand of residents of the City;

**NOW, THEREFORE,** the Cabinet of Addis Ababa City Government, in accordance with Article 23(1) (f) of the Revised Charter Proclamation No.361/2003, issued this Regulation as follows.

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፳፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአዲስ ዙ-ፓርክ ማዕከል ደንብ ቁጥር ፶፪/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፣

፪. **"ማዕከል"** ማለት በዚህ ደንብ የተቋቋመ የአዲስ ዙ-ፓርክ ማዕከል ነው፣

፫. **"ቦርድ"** ማለት የማዕከሉ ሥራ አመራር ቦርድ ነው፣

፬. **"ሥራ አስኪያጅ"** ማለት ማዕከሉን የሚመራ የበላይ ኃላፊ ነው፣

፭. **"የዱር እንስሳ"** ማለት ማናቸውም በፓርክ ሊታቀፍ የሚችል የዱር እንስሳ፣ አዕዋፍ፣ ሕፃናቶቻቸውንና ዕንቁላላቸውን ይጨምራል፡፡

### ፫. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

### ፬. መቋቋም

፩. የአዲስ ዙ-ፓርክ ማዕከል (ከዚህ በኋላ "ማዕከል" እየተባለ የሚጠራ) ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፣

፪. ማዕከሉ በሥራ አመራር ቦርድ የሚመራ ሆኖ ተጠሪነቱ ለከንቲባው ጽህፈት ቤት ይሆናል፡፡



## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as "The Addis Zoo Park Center Regulation No. 52/2012".

### 2. Definitions

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1. **"Government"** means the Addis Ababa City Government;
2. **"Center "** means the Addis Zoo Park Center established in accordance with this Regulation;
3. **"Board"** means the Management Board of the Center formed in accordance with this Regulation;
4. **"Manager"** means an official superiorly directing the Center;
5. **"Wild Life"** means any wild animal, bird, including their offspring and eggs accommodated in the park.

### 3. Scope of Application

This Regulation shall be applicable in the City Government of Addis Ababa.

### 4. Establishment

1. The Addis Zoo park Center (herein after referred to as "Center" is hereby established having distinct legal personality;
2. The Center, being directed by the Management Board, shall be accountable to Office of the Mayor.



## ክፍል ሁለት

## ዓላማ፣ አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር

**፭. ዓላማ**

የማዕከሉ አላማ የከተማውን የዱር እንስሳት ሀብት እንዲለማ፣ እንዲጠበቅና ዘላቂነት ባለው መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረግ ይሆናል፡፡

**፮. የማዕከሉ አደረጃጀት**

ማዕከሉ፡-

፩. የሥራ አመራር ቦርድ፤
፪. ዋና ሥራ ዳይሬክተር፤
፫. እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዳይሬክተር፤
፬. አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

**፯. የማዕከሉ ስልጣንና ተግባር**

ማዕከሉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. በዱር እንስሳት አረባብ፣ ጥበቃ፣ ጤና፣ አመጋገብ፣ አኗኗር እንዲሁም ተያያዥ በሆኑ ሥነ- ሕይወታዊና ሥነ-አካላዊ ጉዳዮች ላይ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል፤
፪. ለማዕከሉ በተከለለ ቦታ ላይ በዙ-ማስተር ፕላን መሠረት የመሬት አጠባበቅና ዲዛይን ስራዎችን ያከናውናል፤
፫. የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን ያለማል፣ ያስተዳድራል፣ ህገወጥ ተግባራት እንዳይፈፀሙባቸው ይከላከላል፤
፬. ለነዋሪዎች የመዝናኛ አገልግሎት ይሰጣል፤
፭. የዱር እንስሳት ጥበቃ ልማትና አጠቃቀም በሚመለከት የስልጠና ፕሮግራም ያካሂዳል፤ ወቅታዊ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፣ ተሞክሮን ይቀበላል፣

## OBJECTIVE, ORGANIZATION, POWER AND FUNCTION

**5. Objective**

Objectives of the Center Shall be to cause the development, Conservation, and sustainable utilization of the wildlife resource of the City.

**6. Organization of the Center**

The Center shall have:

1. Management Board;
2. General Director;
3. Deputy Director, as may be necessary;
4. The necessary staff members.

**7. Power and Function of the Center**

The Center shall have the following powers and functions to:

1. conduct study and research on wildlife reproduction, conservation, health, feeding, livelihood, as well as related biological and biophysical matters;
2. carryout activities of land preservation and design concerning the site of the Center according to the zoo master plan;
3. develop and administer wildlife conservation areas; protect same from illegal activities;
4. provide recreational service to the public;
5. conduct training program on wildlife preservation, development and utilization; gather up-to-date information thereof, distribute to the users and share experience;




**PART TWO**

፮. ጎብኚዎችን በመሳብ የቱሪዝም ኢኮኖሚ እንዲጠናከር ያደርጋል፤

፯. ውበትና ጥምር ጥቅም ያላቸው ዕፅዋትን ይመርጣል፣ ያራባል፣ ያስፋፋል፣ ይንከባከባል፣ ለመሰል ፓርኮችም ተሞክሮውን ያካፍላል፤

፰. በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ የቴክኒክ እርዳታና ሌላም ድጋፍ ሊሰጡ ከሚችሉ አካላት ጋር ግንኙነት ይመሰርታል፤

፱. የማዕከሉን ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ለቦርድ አቅርቦ በማስፈቀድ በተግባር ላይ ያውላል፣ ወቅታዊ የዕቅድና የበጀት አፈጻጸም ሪፖርት ለቦርዱና ለሚመለከታቸዉ አካላት ያቀርባል፤

፲. የማዕከሉን የአጭር፣ መካከለኛና የረዥም ጊዜ የልማት ፕሮጀክቶችንና የድርጊት መርሀ ግብር በመቅረጽ ለቦርድ አቅርቦ በማስጸደቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፩. በማዕከሉ የሚፈጠረዉን የእንስሳት ፍግና የዕፅዋት ተረፈ ምርቶችን ወደ ተፈጥሮ ማዳበሪያና ቀልዝ በመለወጥ ጥቅም ላይ እንዲዉል ያደርጋል፤

፲፪. ተግባራቱ ከአካባቢዉ ሥነ ምህዳር የሚስማሙ፣ የአገራችንን ሥነ ምህዳር የሚወክሉና ከአካባቢ ጥበቃ ዓላማዎች ጋር እንዲስማሙ አድርጎ ይፈጽማል፤

፲፫. ለሚሰጠው አገልግሎት ተገቢውን ዋጋ ያጠናል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፬. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ በህግ መሰረት ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፲፭. አላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

6. cause the tourist economy strengthened by attracting visitors;
7. select, reproduce, expand and care ecstatic plants with multiple uses; share its experience to other parks;
8. establish relationship with all bodies having the potential of providing technical and other assistance for wildlife conservation;
9. prepare and submit to the Board annual activity and budget plan of the Center; implement same upon approval by the Board; submit timely execution report of activity and budget to the Board and other concerned bodies;
10. submit the short, medium and long term development projects and activity plan of the Center to the Board; implement same upon approval by the Board;
11. cause the dung of animals and by-products of plants in the Center to be converted into natural fertilizer and bio-gas and utilized;
12. perform functions in a way compatible to the ecology of the surrounding and representing the ecological zones of the country as well as objectives of environmental protection;
13. study and implement appropriate service charge up on approval by the concerned body;
14. own property, enter into contract as per law; sue and be sued in its own name;
15. Carryout such other activities as are necessary for the fulfillment of its objectives.





፰. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር</u>

የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩.ማዕከሉን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፪.የማዕከሉን ዓመታዊ የስራና የበጀት ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፫.ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ማዕከሉን ይወክላል፤

፬. በማዕከሉ ስም የባንክ ሂሳብ እንዲከፈት ለፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ጥያቄ ያቀርባል፣ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ሂሳብ በትክክል መያዙን ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል፤

፭. በተፈቀደው በጀት መሰረት ገንዘብ ወጪ እንዲሆን ያደርጋል፤ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤

፮. የማዕከሉን የስራ እንቅስቃሴና የሂሳብ ሪፖርት በወቅቱ አዘጋጅቶ ለቦርድ ያቀርባል፤

፯. ከውጭና ከሀገር ውስጥ ተቋማት ጋር የሚደረጉ የምርምርና ሌሎች የአቅም ግንባታ ትብብር ውሎችን ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፰.አግባብ ባለው ህግ መሰረት የማዕከሉን ሰራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

፱. በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**፱. <u>የምክትል ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>**

የማዕከሉ ምክትል ዳይሬክተር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩.የማዕከሉን ዓመታዊ ዕቅድ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ዋና ዳይሬክተሩን ይደግፋል፣ ተባብሮ ይሠራል፤



**8. <u>Power and Function of the General Director</u>**

General Director of the Center shall have the following powers and functions:

1. superiorly coordinate and administer the Center;
2. prepare the annual action and budget plan of the Center; and implement same upon approval;
3. represent the Center concerning the relationship with third parties;
4. request the Finance and Economic Development Bureau to open bank account; implement upon approval; ensure and check that the account is properly maintained;
5. cause finance withdrawn as per the allocated budget; and ensure the proper utilization of same;
6. timely prepare and submit the performance and financial report of the Center to the Board;
7. present to the Board and implement upon approval contracts of research and other capacity building cooperation with domestic and foreign institutions;
8. hire, administer and dismiss staffs of the Center in accordance with the relevant law;
9. Perform other related functions given to it by the Board.

**9. <u>Power and Functions of the Deputy Director</u>**

Deputy Director of the Center shall have the following powers and functions:

1. support the General Director and work in cooperation regarding implementation of the annual plan of the Center;

፪. ዋና ዳይሬክተሩ በተለያየ ምክንያት ሥራዉን መወጣት በማይችልበት ወይም በዋና ዳይሬክተሩ ሲወከል ተክቶ ይሠራል፤

፫. ሌሎች የማዕከሉን ዓላማ ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ በዋና ዳይሬክተሩ ወይም በቦርዱ የሚሰጡ ተግባራትን ይፈጽማል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለ ቦርድ አመሰራረት፣ ስልጣንና ተግባር

**፲. ስለቦርዱ መቋቋምና የስራ ዘመን**

፩.ማዕከሉ ከ፯ እስከ ፱ የሚሆኑ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ይኖሩታል፤

፪.ከሚከተሉት ተቋማት ውስጥ በከንቲባው የሚሰየሙ ሰዎች የስራ አመራር ቦርድ አባላት ይሆናሉ፡-

ሀ. ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽህፈት ቤት ተወካይ..................ሰብሳቢ፤

ለ. ከአዲስ አበባ ከተማ ስራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት ተወካይ...........................አባል፤

ሐ.ከአዲስ አበባ ከተማ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ተወካይ.................................አባል፤

መ.ከአዲስ አበባ ከተማ ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ተወካይ...................አባል፤

ሠ.ከአዲስ አበባ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተወካይ......................አባል፤

ረ. ከኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ተወካይ...........................አባል፤

ሰ. ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተወካይ........አባል፤

ሸ.የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር (ያለድምጽ)...........................አባልና ፀሐፊ፤

ቀ.እንዲሁም ሌላ አንድ እንደአስፈላጊነቱ በከንቲባው የሚሰየም አባል ይሆናል፡፡

2. represent the General Director in cases of his incapacity to perform duty due to different reasons or where the General Director so authorizes;
3. perform such other duties necessary to achieve objectives of the Center designated by the General Director or the Board.

## PART THREE
## ESTABLISHMENT, POWER AND FUNCTION OF THE BOARD

**10. Members and Terms of Office of the Board**

1. The Center shall have 7-9 management board members;
2. Persons assigned by the Mayor from the following institutions shall be members of the management board:

a. Representative from Addis Ababa City Government Office of Mayor…………………………......Chairperson;

b. Representative from Addis Ababa City Manager Office ……………………Member;

c. Representative from Addis Ababa City Bureau of Culture and Tourism.…..Member;

d. Representative from Addis Ababa City Bureau of Communication Affairs…………………..……....Member;

e. Representative from Addis Ababa City Environmental Protection Authority ………………………………....….Member;

f. Representative from Ethiopian Wildlife Development and Conservation Authority…………………..…..…..Member;

g. Representative from Addis Ababa University……………………….....Member;

h. General Director of the Center (without vote) ……………………. Member and Secretary;

i. One other member assigned by the Mayor, where found necessary.

፫. የቦርዱአባላት የስራ ዘመን ፭ አመት ሆኖ አንድ የቦርድ አባል ለሁለተኛ ጊዜ ሊሰየም ይችላል፡፡ ሆኖም አንድ የቦርድ አባል በተለያየ ምክንያት የቦርድ አባልነቱን ያቋረጠ እንደሆነ ሌላ የቦርድ አባል ለቀሪው ጊዜ ሊወከል ይችላል፡፡

## ፲፩. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የማዕከሉን አሰራር፣ፖሊሲዎችና መመሪያዎች መርምሮ ያፀድቃል፤

፪. የማዕከሉን አመታዊ ዕቅድና በጀት ተዘጋጅቶ ሲቀርብለት በመመርመር ለሚመለከተው አካል እንዲቀርብ ይወስናል፤

፫. ለማዕከሉ አፈጻፀም ቅልጥፍና እና ጥራት እገዛ የሚያደርጉ ባለድርሻ አካላት ተግባራቸውን በአግባቡ እየፈፀሙ መሆኑን በማረጋገጥ ተገቢውን ሁሉ እንዲያከናውኑ ድጋፍ ይሰጣል፤

፬. የማዕከሉን የሥራ አፈፃፀም በመገምገም በወቅቱ ሪፖርት ለከተማው ከንቲባ ጽህፈት ቤት ያቀርባል፡፡

## ፲፪. <u>የቦርዱ ስብሰባ ስነ-ስርዓትና ተጠያቂነት</u>

፩. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም ሰብሳቢው አስቸኳይ ሁኔታ ገጥሟል ብሎ ባመነ ጊዜ ሁሉ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤

፪. ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ ሲገኝ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤

፫. ቦርዱ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፣ ሆኖም ድምፁ እኩል ከሆነ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ የቦርዱ ውሳኔ ይሆናል፤

3. The term of office of the Board shall be five years and a member shall be assigned for another term. If a member of the Board terminates due to different reasons before the term, another member of the Board may be appointed for the remaining period of time.

## 11. <u>Power and Function of the Board</u>

The Board shall have the following power and functions:

1. examine and approve the work procedures, policies and directives of the Center;
2. examine the annual activity and budget plan of the Center prepared and presented to it; decide same to be submitted to the concerned body;
3. ensure and support stakeholders that are contributing to the effectiveness and quality of the Center perform their respective function properly;
4. submit periodical report to Office of the Mayor by evaluating performance of the Center.

## 12. <u>Meeting Procedure Accountability of the Board</u>

1. The Board shall meet once in a month; however, the Chairperson may call an extra ordinary meeting;
2. It shall constitute a quorum while more than half of the members are present at a meeting of the Board;
3. Decision of the Board shall be passed by majority vote, and in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote;

፬. በቦርዱ የሚተላለፍ ውሳኔ ህግን የሚፃረር ሆኖ ሲገኝ በውሳኔው ተካፋይ የሆነ ማንኛውም አባል በግልም ሆነ በጋራ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ ሆኖም የልዩነት ሐሳቡን ያሰመዘገበ አባል ከተጠያቂነት ነፃ ይሆናል፤

፭. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ስነ ስርዓት ውስጠ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፫. የበጀት ምንጭ

የማዕከሉ የበጀት ምንጭ፡-

፩. በአስተዳደሩ ከሚመደብ በጀት፣ እና

፪. ከተለያዩ ህጋዊ ምንጮች ከሚገኝ ገቢ፣ ይሆናል፡፡

### ፲፬. የሂሣብ መዛግብት አያያዝ

፩. የማዕከሉ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች አያያዝና አጠባበቅ የከተማው አስተዳደር የፋይናንስ ህጎች የተከተሉ ይሆናሉ፤

፪. የማዕከሉ የተሟላ እና ትክክለኛ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤

፫. የማዕከሉ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነ ዶች በከተማው አስተዳደር ዋናው ኦዲተር መስሪያ ቤት በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ይመረመራሉ፡፡

### ፲፭. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ማዕከሉ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚረዳ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

### ፲፮. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ ለማስፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

4. Each member of the Board who participated in the decision shall be jointly and severally liable where the decision is contrary to law. However, a member who had dissenting position shall not be made liable;
5. Without prejudice to the provisions of this Article, the Board may issue its own rules of internal regulation regarding meeting.

## PART FOUR
## MISCELLANEOUS PROVISION

### 13. Source of Budget

The source of budget for the Center shall be from፡

1. Budget allocated to it by the City Government; and
2. Revenue acquired from other legal sources.

### 14. Keeping of Books of Account

1. The keeping and maintenance of the accounts and finance related documents of the Center shall be complied with the finance administration laws of the City Government;
2. The Center shall keep complete and accurate books of account;
3. The books of account and financial records of the Center shall be inspected by auditors to be assigned by Office of the Auditor General of the City Government.

### 15. Power to Issue Directive

The Center may issue directive to implement this Regulation.

### 16. Obligation to Cooperate

Any person shall have the duty to cooperate for the implementation of this Regulation.

**፲፯. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፲፰. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከመስከረም ፲፩ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**

**መስከረም ፲ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም**

**ኩማ ደመቅሳ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**17. Inapplicable Laws**

Any Regulation, directive or customary practice which is inconsistent with matters covered in this Regulation shall have no effect.

**18. Effective Date**

This Regulation shall enter into force as of the 21st of September, 2012.

**Done at Addis Ababa,**

**20th Day of September, 2012**

**Kuma Demeksa**

**Mayor of Addis Ababa City**